# የሃገርና የህዝባችን ጉዳይ ይመለከተናል ለምትሉ ውድ ኢትዮጵያውያን በሙሉ፤

ላለፉት አሥራ ስምንት ዓመታት አገራችን ታይቶ በማይታውቅ፤ አገርን፤ ዘርን፤ እንዲሁም ታሪክን እጅግ የሚያሳፍር አገዛዝ ሥር መውደቋና፤ አሁንም በቀላሉ ልትላቀቀው ያልቻለችው አገር በቀል ጠላት እንዳጋጠማት፤ ማንም አገሩና ህዝቡን አፈቃሪ ዜጋ ሁሉ የሚገነዘበው ሃቅ ነው።

ያለመታደል ሆኖ፤ ወገኖቻችን በደርግ ሥርዓት አሰቃቂ ጭፍጨፋ ተርፈው፤ ሃዘንን የሚያስረሳና የተሻለ ሥራዓት እናያለን ስንል፤ "ትሻልን ስድጀ፤ ትብስን አመጣሁ" እንዲሉ ዛሬም ሰውንም፤ አገርንም ከሚያጠፋ የባሰ ሥርዓት ሥር ወድቅን።

ሆኖም አንድ ሥርዓት ዘላለማዊነት እንዳሌለው ሁሉ፤ ተወደደም ተጠላም ነገም ይህ ሥራዓት ያልፋል። ይሁን እንጅ፤ በአገርና በህዝብ ላይ ከአስከፊ ሥራአት ጋር እጅና ጓንት ሆነው ወንጀል የሰሩ ፈጽሞ ከፍርድ እንደማያመልጡ በታሪክ እንዳየነው ሁሉ፤ ከዚህ ሥራዓት ጋርም በመተባበር ግፍ ሰርተው ያለፉና፤ ሥርዓቱ ከማለፉ በፊት በተለያየ የግላቸው ምክንያት የተለዩ ሁሉ ፍጽሞ ከፍርድ ነፃ መሆን እንደማይችሉ ከወዲሁ መረዳት አለባቸው።

ስለሆነም፤ የወያኔ/ኢሃዴግ ሥርዓት ቀንደኛ ተዋኒያን፤ የአንድ ወቅት ፕራይም ሚኒስተር፤ በሌላም ወቅት የመከላከያ ሚኒስተር ሆነው፤ አገራችንን ያለ ባህር በር ያስቀሩ፤ በወገኖቻችን ላይ የግፍ ጭፍጨፋ ያደርሱ፤ የነበሩት አቶ ታምራት ላይኔ፤ እጃቸው ከተነከረው ደም ሳይጸዳ፤ ወቅት ያነሳኝ ዳግማዊ ሃዋሪያው ጳውሎስ ነኝ በማለት፤ የበደሉትን ሕዝብና አገር፤ እንዲሁም ሰለፈጸሙት ግፍ በግልጽ ይቅርታ ሳይጠይቁ አሜሪካ ውሥጥ በመዘዋወር ሌላ ግፍ ሲሰሩ ይታያሉ።

እኒሁ ሰው ይህን ተመሳሳይ ሥራቸውን በማራዘም ከዛሬ አርብ ጀምሮ እስከ እሁድ ድረስ ሴንት ሊዊስ በምተገኘው ወንጌላዊት ቤተ/ክርስቲያን ስለሚገኙ፤ ቤተ-ክርስቲያን የነብሰ ገዳይ መደበቂያ መሆን እንደሌለባት ለመግለጽ የተቃውሞ ሰልፍ እናደርጋለን። ማንም ለወገኖቹ ለህግ የበላይነት የቆመ ዜጋ ሁሉ በዚህ የተቃውሞ ድምጽ ማሰማት እንድትተባበሩን በትህትና እንጠይቃለን።

ቦታ፡- 9116 Lacland Ave. Overland, MO. 63114

ቀን፦ አርብ October 09, 2009 ከ 3፡00pm **to 6:00pm**

ቅዳሜ October 10, 2009 ከ 10፡00Am 2፡00**pm**

የአገራችንና የሕዝባችን ስቀቃ ያገባናል ዬምንል ኢትዮጵያውያን።